ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ግንቦት 0 9 2015

ቁጥር/REF NO: 1/256/መ29/15

**ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች**
**ለሁሉም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት**
**ለሁሉም የክልል ትምህርት ቢሮዎች**
**<u>ባሉበት</u>**

**ጉዳዩ፡-** <u>የአገር አቀፍ ፈተና ቀናትና መርሃ-ግብር ስለማሳወቅ</u>

በትምህርት ጥራት ላይ ከምንወስደው ወሳኝ ጉዳዮች ጐን ለጐን ከፈተና አስተዳዳር ስርዓት ጋር ተያይዞ ያሉ ክፍተቶች በቀጣይ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ዘላቂ መፍትሄ እስኪፈጠር ድረስ የተለያዩ ስልቶችን መተግበር እንዳለብን በተደረሰው ስምምነት መሠረት በዚህ የትምህርት ዓመት ማጠቃለያ የሚኖሩ ጉዳዮች በሚከተሉት ቀናት እንዲከናወኑ መወሰኑን እገልጻለሁ፡፡

1ኛ/ በ2014 የ12ኛ ክፍል አጠናቀው ፈተና በመውሰድ በልዩ ሁኔታ የሬሜዲያል ኘሮግራም ተጠቃሚ ለሆኑ ተማሪዎች ለአንድ ሴሚስተር የተሰጠው ትምህርት በማዕከል የጋራ ፈተና ተዘጋጅቶ ለተቋማት እንዲላክ፤ ተቋማት ፈተናውን የማስተዳደር ውጤት የመግለፅና በ2016 ፍሬሽማን ኘሮግራም ለመከታተል ብቁ ሆነው የተገኙት (ማለትም በተቋማት የውስጥ ፈተና 50 ከመቶ፣ በማዕከል የተዘጋጀው ፈተና 50 ከመቶ) ተደምሮ በድምሩ 50 ከመቶና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡቱን እንዲያሳወቁ፣ ይህ አጠቃላይ ሂደት እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ እንዲጠናቀቅ፡፡

2ኛ/ በ2015 ዓ.ም የመውጫ ፈተና ለመውሰድ የተመዘገቡ በግልና በመንግስት ተቋማት የሚገኙ እጩ ምሩቃንና ባለፉት ዓመታት የህግ መውጫ ፈተና ወስደው የማለፊያ ውጤት ያላስመዘገቡት ተማሪዎች የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች የመፈተኛ ማእከላት ውስጥ ፈተናው ከሐምሌ 3 እስከ 13 ባሉት ቀናት ተሰጥቶ እንዲጠናቀቅ፡፡

3ኛ/ የ2015 የ12ኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና ከሐምሌ 19 እስከ 30 የሚሰጥ ሆኖ የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ከሐምሌ 15 ቀን ጀምሮ ለዚሁ ሥራ ብቻ ዝግጁ እንዲሆኑ፡፡

በተጨማሪም እንደ አገር ዓመታዊ የትምህርት ካላንደር ከ2016 ጀምሮ ለማስተካከል ሁሉም ተቋማት ፕሮግራሞቻቸውን በዚሁ ማዕቀፍ እንዲያስተካክሉ ከአደራ ጭምር አሳስባለሁ፡፡

**ከሠላምታ ጋር**

በየኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

**ግልባጭ፡-**
ለሚኒስትር ጽ/ቤት
ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት [ከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ]
ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት [አጠቃላይ ትምህርት ልማት ዘርፍ]
**<u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>**
ለኢትዮ ቴሌኮም
ለኢትዮጲያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት
ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን
ለኢትዮጲያ አየር መንገድ ግሩፕ
ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት
ለትምህርትና ሥልጠና ባለስልጣን
**<u>አዲስ አበባ</u>**